# ከእውነት ሊወድቁ ያሉ ኮብላዮች ላይ የሚታዩ ምልክቶች ምንድን ናቸው?

መቼም እምነት ለሁሉ አይሆንም፥  ጉዞ የጀመረ ሁሉ አይጭርስም የተጥሩ ብዙዎች ቢሆኑም የተመረጡት ግን ጥቂቶች ይሆናሉ። አብረውን ማእድ ያጣጣሙ ሁሉ አብርውን አይጠነክሩም ቤተክርስቲያን የወለደቻችው ሁሉ አይዞሽ አይሏትም ያሳደግቻችው ሁሉ አያግዟትም ስለዚህ አንዳንዶች እንደጠማማ ቀሰት ሊገልበጡ ግድ ይሆናል፤ በዚህ ጊዜ በቤት የሚኖሩ መኖሪያቸውን ያለቀቁ እንደምን ሊሆኑ እና ምላሽ ሊሰጡ ይገባችዋል የሚለው ጥያቄ ይነሳል በሂደት ሊከሰቱ የሚችሉ ነገሮችን  ካወቅናቸው ምላሻችን ምን መሆን እንደሚገባው ለማን ምን መናገር እንደሚገባን ጭምር እናውቃለን ።ሌሎችን ልንረዳ ስንዘጋጅ ራሳችንን አስቀድመን እንዴት ልንጠብቅ እንደሚገባን ማወቅ አለብን እንግዲህ እናንተ፥ ወዳጆች ሆይ፥ ይህን አስቀድማችሁ ስለምታውቁ፥ በዓመፀኞቹ ስሕተት ተስባችሁ ከራሳችሁ ጽናት እንዳትወድቁ ተጠንቀቁ፤ 2ኛጴጥ 3፡17 እንደሚል ሌሎችን ሊረዳ የሚንሳ የራሱን መከላከያ ማጥለቅ ግድ ይለዋል ። ካላጠለቀ ሊረዳ የተዘጋጀ ሰው ሳይሆን ሊረዱ የሚገባቸውን የሚጠራ ሰው ሊሆን ይገባዋል።  አለበለዚያ ተጨማሪ አደጋ ውስጥ ያለ ተደረጎ ሊቆጠር ይገባዋል። ይህ ትምህርት በስጋቸው ድካም ወደ አለም የገቡት ላይ ትኩረት አያደርግም ነገር ግን ከእውነት ፍቅር  ፈቀቅ ማለት የጀመሩ ሰዎችን  ላይ ያተኩራል.።  እነዚህ አይነቶቹ የሚከተሉትን ምልክቶች እናይባቸዋለን፦

- ሊወድቁ ያሉ ሰዎች ከመሰጠታችው ይወርዳሉ ፦ከመጋቢ መራቅ ፣ራሳቸውን ያሰማራሉ ፣ከጸሎት፣ከአገልግሎት፣ከህብረት ከምሳስሉት ነገሮች ራሳቸውን ያርቃሉ
- ሊወድቁ ያሉ ሰዎች አስቀድመው ከሚታወቁበት አቋማቸው ይንሸራተታሉ፤ ይተቻሉ፣ያጉረምርማሉ ፤ምናለበት ያበዛሉ ፤ተቆርቋሪ መስለው ይታያሉ እና ይደፍራሉ
- ሊወድቁ ያሉ ስዎች ግራመጋባት ውስጥ ይገባሉ ሌሎችንም ግራ ያጋባሉ፣ሰው ለይተው ይቀርባሉ ጥያቄ ያነሱና እነሱ ራሳቸው ያስትምራሉ የሌሎችን መልስ ያጣጥላሉ።

ከላይ እንደተመለከትነው ሊወድቁ ያሉ ሰዎች በመጀመሪያ ከመሰጠት ከፍታቸውን ራሳቸው ይለቃሉ ብዙውን ጊዜ ውድቀት ቀስ በቀስ በመንሸራተት የሚመጣ ስለሆነ ቶሎ አይታወቃቸውም በሂደትም ወደ ቀጣዩ ደረጃ ይህም አስቀድሞ የነበራችው

አቋም ወደ መለወጥ ይመጣሉ ማለት ነው ፣ከዚያም የሚታወቁበት የከበረ ነገር ሁሉ የእነሱ ላይሆን ይነጠቃሉ ፣ስለዚህም በህይወታቸው ግራ መጋባት ይታያል ጥያቄዎችንም ያነሳሉ ይህም የተለምደው ሂደት ነው። ይህን ማወቅ እየወደቁ ያሉ ህይወቶች እንዴት እና በማን ሊረዱ እንደሚገባቸውና እንዲመከሩ እንዲገስጹ አቅሙ ካላችው እንዲዘልፉ ይቻላቸው ዘንድ ያመቻቻችዋል ፤ በሂደትም ከወደቁበት ይነሱና ወደ ከፍታቸው ይመለሳሉ ይህ ካልሆነ ደግሞ በተቃራኒው በቤተክርስቲያን በክብር የኖሩበትን ዘመናት እንደሞኝነት ወደሚቆጥሩበት ጊዜያቸውን እንዳባከኑ በመናገር ወርቃቸውን ያደብሳሉ፣ ይቀላሉ ፣ይረክሳሉ ፣ራሳቸውን ይሸጣሉ ባብዛኛው የሚገዛቸው አያገኙም ስለዚህም ይንቅዠቅዣሉ ሰው ያጣላሉ ፣ይከሳሉ፣ ይከሰሳሉ ቡድን ይመሰርታሉ አስቀድሞ ከነበሩበት ቡድን ይልያሉ ያጉርምርማሉ በሁሉም በሚባል ደረጃ ይነቅፋሉ ይተቻሉ ይሄ ሁሉ ግራ መጋባታቸውን ያሳያል።

ይህን ለማየት ምሳሌ የሚሆነን ሰው፦ አቤሴሎም እንመልከት

1. **ኮብላዮች የኩብለላ ታሪክ ያላችው ናቸው** ፦ አቤሴሎም ኰብሎሎ ወደ ጌሹር ሄደ፥ በዚያም ሦስት ዓመት ያህል ተቀመጠ።በአንድ ወቅት ጥፋት ከወንድሞች እና እህቶች ያራቃቸው በብዙ እንባ እና ጸሎት ከእግዚብሔር ጉባኤ የተቀላቀሉ ሁሌ ሊያሳስባቸው የሚገባው ነገር ቢኖር ይህ ልምድ ሆኖ ገባ ወጣን እንዳይለምዱ መሆን ይገባዋል።ከአቤሴሎም የምንማረው ከኩብለላው የተመለሰ ቢሆንም ክፉ ልማድ( ልምምድ) ውስጥ አልፏል በመታደስ እና በእውነተኛ ንስሃ ሊጠፋ የሚገባው ድፍረት አለበት ።በተለይ ይህ የኩብለላ ልምምድ በቅርብርብ ወደ ሌሎች ያልፋልና በወዳጅነት በጉርብትና እንዲሁም በአድናቆት እንዳይጋባብን ልንጠነቀቅ ይገባል።ኮብላይ ተጽናነቶ ለመቆየት ያህል የውጪ ምግብ ለመልመድ ይገደዳል፣ ከሌሎቸ ጋር ህብረት ያደርጋል ፣ራሱን ያመሳስላል ይመስላል ይህ ወደ ቤቱ ሲመለስ በቶሎ ላይለቀው ይችላል አልፎም መልሶ ሊጠልፈው እና ሊጥለው ሁሉ ይችላል።

2. **ኮብላዮች በምህረት የሚቀበላቸውን ይንቃሉ፦** በምህረት የተቀበሉን ታላላቆች ጥፋታችንን እረስተው ሳየሆን በእግዚአብሄር ተጽናንተው ነው።ንጉሡም ዳዊት ስለ አምኖን ሞት ተጽናንቶ ወደ አቤሴሎምይሄድ ዘንድ እጅግ ናፈቀ። እንደሚል ደግሞ ደጋግሞ መበደል እጅግ አሳዛኝ ልምምድ ነው፣ ካሳን ለሚናፍቅ ህዝብ ድጋሚ በደል ተገቢ አይደለም ። አለመታዘዝን

ለመበቀል የማይነሳ ድጋሚ  መበደሉ አይቀሬ ነው፤ ከዚህ በደል የሚያወጣን መታዘዛችን መፈጸሙ ብቻ ነው ። በምህረት የተቀበለን እግዚአብሔር እና ሕዝቡ ንጹሐን እንደሆናችንን እርግጠኛ መሆን ይፈልጋሉ፣ ስለዚህ ሃዘናችንን ቁጣችንን ትጋታችንን ጥለነው ስለመጣነው ነገር ያልን ቁጣ እና  ስለቆምንበት ነገር ቅንዓታችንን ናፍቆታችንን  የዘውትር የፍርሃት ኑሮአችንን ሊያዩት ይፈልጋሉ ። እነሆ፥ ይህ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ኀዘን እንዴት ያለ ትጋት፥ እንዴት ያለ መልስ፥ እንዴት ያለ ቁጣ፥ እንዴት ያለ ፍርሃት፥ እንዴት ያለ ናፍቆት፥ እንዴት ያለ ቅንዓት፥ እንዴት ያለ በቀል በመካከላችሁ አደረገ። በዚህ ነገር ንጹሐን እንደ ሆናችሁ በሁሉ አስረድታችኋል።

3. **ኮብላዮች ብቃታቸውን ችሎታቸውን እና ጸጋቸውን ወይም ተወዳጅነታቸውን ይጠቀሙበታል፦** ብቁ መሆናችን ነውር የሌለን አድርጎ ሊያሰቆጠርን ይችል ይሆናል፤ ትምክህት እና ኩራት ሆኖ የውድቀት ምክንያት እንዳይሆን ልንጠነቀቅ ይገባል።አቤሴሎም ልጅ የልኝም ብሎ መታሰቢያውን ገነባ ውጤቱ ግን ሌላ ሆነ። ዛሬ በኢየሩሳሌም ከሚጎበኙ የቱሪዝም ስፍራዎች አንዱ የአቤሴሎም ሃውልት  ነው ምክንያቱም ደግሞ የሰራው ነውር ነው ስለዚህም የእስራኤል ብላቴኖቸ የአቤሴሎምን ሰራ(ነውር)  እንዳይደገም ድንጋይ እየወረወሩበት ያልፋሉ።

4. **ኮብላዮች እንዳልተቀበሉ ሆነው ይመካሉ፦** እስራኤልም ሁሉ ዘንድ እንደ አቤሴሎም በውበቱ የተመሰገነ ሰው አልነበረም፤ ከእግሩ እስከ ራሱ ድረስ ነውር አልነበረበትም። እንዲሁ መኖሪያውን እና ስፍራውን ስለለቀቀው የቀደመው መልአክ በተነገረበት ክፍል በውበትህ ኮርተሃል የሚል  አለ። አቤሴሎም በውጪ ነውር የሌለበት የሚመስል ነውረኛ ነበር ፣ባደባባይ በእስራኤል አይን ሁሉ ፊት የአባቱን አልጋ አርክሶ እጅግ አሳፋሪነቱን አሳየ ፤ በእህቱ ላይ በተሰራ ነውር ቂም የያዘ መስሎ ተነሳ ነገር ግን አባቱን አሳፈረው። ጥፋትን ለማረም የተነሳው የሚበልጥ ርኩሰት ሰሪ ሆነ። ከዚህ የምንማረው ነውር አልባ ናቸው ተበድለዋል ብለን ምንሟገትላቸው ፣ የምንደግፋቸው ሰዎች ነገ እነርሱ የሚፈጽሙት በደል እን ርኩሰትን በአደባባይ እንኳ ከማድረግ እንደማይመለሱ ያስተምረናል።

5. **የኮብላይ ወዳጆች እርሻቸው ይቃጠላል፦**  ኢዮአብም ተነሥቶ ወደ አቤሴሎም ወደ ቤቱ መጣና፦ ባሪያዎችህ እርሻዬን ስለምን አቃጠሉት?

አለው።የኮብላይ ወዳጆች እንደ ኢዮአብ ሳይሆኑ አይቀሩም ለኃጢአተኛ ሞገስ ቢደረግለት ጽድቅን አይማርም፤ በቅኖች ምድር ክፉን ነገር ያደርጋል፥ የእግዚአብሔርንም ግርማ አያይም።ኢሳ 26፡10 እንደሚል ቃሉ ኮብላይ የወዳጁን እርሻ ያቃጥላል ብዙ የኮብላይ ወዳጆች እርሻ ነዷል ቤታቸውን እና ልጆቻቸውን በለቀቁ የኮብላይ ወዳጆች መኖሪያ ቤት የተዘራ እንክርዳድ ቤተክርስቲያንን ብዙ ዋጋ አስክፍሏታል ኢዮአብም እርሻውን አጣ ።በአንድ ወቅት ለሚቀርበው እና መስካሪ እንደሆነ ለቆጠረው ግን ኮብላይ ለነበረ ቤቱን የለቀቀ ሰው ከጉዳት መልስ ተጸጽቶ ቤቴን የጦር ማዘዣ አድርገህ ቤተክርስቲያንን ወጋህ ብሎ ኮብላዩን እንዳሰናበተ ሰምቻለሁ።

6. **ከኮብላይ በፊቱ የሚሮጡ አድናቂዎችን ያፈራል፦**ከዚህም በኋላ አቤሴሎም ሰረገላና ፈረሶች፥ በፊቱም የሚሮጡ አምሳ ሰዎች አዘጋጀ።2ሳሙ 15፡1 ኮብላይ ብዙ ጊዜ የሃምሳ አለቃ ነው ።ህዝብ አይከተለውም ነገር ግን በሃምሳ ሰው ነውጥ ይፈጥራል ። መሪ ስላልሆነ ከኋላው የሚከተል የለውም ጥቂት ደፋር ሞኞችን (ሞኝ ነገርን ሁሉ ያምናል ብልህ ግ ን አካሄዱን ይመለከታል) ያስቀድማል ።ይነዳችዋል ለምን ብለው የማይጠይቁትን ትእዛዝ ተቀባዮች ይመለምላል።

7. **ኮብላይ እስክታፍር ድረስ ልብህን ለመስረቅ ያከብርሃል ፣ይስምሃል ፣ይጠይቅሃል፣ ዋጋ ይከፍልልሃል፦**ከሌሎች ያላገኘኸውን ክብር እና አድናቆት ያጎርፍልሃል ያኔ ልብህን ታጣለህ ማሰብ ታቆማለህ ማስተዋልህ ይጠፋል ምን ሆኜ ነበር እስክትል ድረስ ተሰርቀህ ትጠፋለህ ቅን ፈራጅ እንዳገኘህ እስኪሰማህ ድርስ ትወደዋለህ ነገርህን ወደ ቤትክርስቲያን መውሰድ ታቆማለህ።ነገርህ እውነትና ቅን ነው፤ ነገር ግን ከንጉሥ ታዝዞ የሚሰማህ የለም ይለው ነበር።አቤሴሎምም፦ ነገርና ክርክር ያለው ሁሉ ወደ እኔ ይመጣ ዘንድ ቅንም ፍርድ እፈርድለት ዘንድ በአገር ላይ ፈራጅ አድርጎ ማን በሾመኝ? ይል ነበር።ሰውም እጅ ሊነሣው ወደ እርሱ በቀረበ ጊዜ እጁን ዘርግቶ ይይዝና ይስመው ነበር።እንዲሁም አቤሴሎም ከንጉሥ ፍርድ ሊሰማ ከእስራኤል ዘንድ በሚመጣ ሁሉ ያደርግ ነበር፤ አቤሴሎምም የእስራኤልን ሰዎች ልብ ሰረቀ።2ሳሙ 15፡4፣5፣6 እነሱም አርብኛውን መሪያቸውን ትተው ሸንጋዩን ተከትልው ጠፉ።

8. **ኮብላይ በጥሩ ምክንያት ይሰወራል** ፦ ጾም እና ጸሎት ላይ እንደቆየ ወይንም

ወደ አንድ ምድረበዳ በሽክም እንደቆየ ይነግርሃል ጨርሶ እንደምጣ እንጂ ሊሰወር ሲል አይነግርህም ምክንያቱም ሴራው እንዳይከሽፍ አጋኖ ለማውራት እንዲመቸው መሰወር ጥሩ ዘዴው ነው።እንዲህም ሆነ፤ ከአራት ዓመት በኋላ አቤሴሎም ንጉሡን፦ ለእግዚአብሔር የተሳልሁትን ስእለት ለመስጠት ወደ ኬብሮን፥ እባክህ፥ ልሂድ።2ሳሙ 15፡7

9. **ኮብላይ ምቹ ቀን ይጠብቃል፦** ኮብላይ ጉዳቱን የተወው፣ በልቡ ያልያዘው መስሎ የመቆየት ባህሪ አለው፣ ነገር ግን በግብዣ ቀን ጉድ ያፈላልበ እንደ ንጉስ ያለ ግብዣ አዘጋጅቶ ያጠቃል።ብግ እሸልታለው ብሎ በጠራው ጉባኤ ነፍሳት ይጨርሳል። አቤሴሎምም እንደ ንጉሥ ግብዣ ያለ ግብዣ አደረገ፤ አቤሴሎምም አገልጋዮቹን፦ አምኖን የወይን ጠጅ ጠጥቶ ልቡን ደስ ባለው ጊዜ እዩ። አምኖንን ግደሉ ባልኋችሁም ጊዜ ግደሉት፥ አትፍሩም ያዘዝኋችሁም እኔ ነኝና በርቱ ጽኑም ብሎ አዘዛቸው።2ኛሳሙ 13፡28

10. **ኮብላይ በመረጠው ጎዳና በስኬት ሳይሆን ተንጠልጥሎ ይደመድማል**፦ የሚገለው ያው ወዳጁ ይሆናል አላማው ተንጠልጥሎ ይቀራል ተሽካሚው ይሰወራል ።አድናቂዎቹ ይበተናሉ በአባቱ ቤት ሃዘን ይሆናል የኮብላይ ወዳጆች ልኮብላዩ ለንስሃ እንኳ ወደ አባቱ ቤት እንዲመለስ አይፈቅዱለትም መጨረሻውን ያፈጥኑታል ምክንያቱም እርሻቸውን አቃጥሎ ነበርና። አቤሴሎም ከዳዊት ባሪያዎች ጋር በድንገት ተገናኘ፤ አቤሴሎምም በበቅሎ ተቀምጦ ነበር፥ በቅሎውም ብዙ ቅርንጫፍ ባለው በታላቅ ዛፍ በታች ገባ፥ ራሱም በዛፉ ተያዘ፤ በሰማይና በምድር መካከል ተንጠለጠለ፥ ተቀምጦበትም የነበረ በቅሎ አለፈ አንድ ሰውም አይቶ፦ እነሆ፥ አቤሴሎም በትልቅ ዛፍ ላይ ተንጠልጥሎ አየሁ ብሎ ለኢዮአብ ነገረው።

መጋቢ ኤልያስ ሽባባው